# VPAS

የቪክቶሪያን
የወሊድ ግዜ/ፔሪናታል
የአስከሬን ምርመራ
አገልግሎት

# ልጅዎ የድህረ ሞት ምርመራ ማድረግ ይኖርበት እንደሆነና እንደሌለበት መወሰን

በልጅዎ ሞት በጣም አዝነናል።

ከልጅዎ ሞት በኋላ የሚያደርጉት ውሳኔ ከሚያከናውኗቸው ውሳኔዎች ሁሉ በጣም ከባድ ይሆናል።

የልጅዎን የድህረ ሞት ምርመራ (የአስከሬን ምርመራ ተብሎ የሚጠራ) ለማድረግ ይወስኑ እንደሆነና እንዳልሆነ እንድታስቡ ለመርዳት ይህ መረጃ ቀርቦልዎታል። አላማችን ለእርስዎ፣ ለቤተሰብዎና ለልጅዎ ተገቢ የሆነ በመረጃ ላይ የተመሰረተ ውሳኔ እንዲወስዱ የሚያግዝዎ ግልጽና ትክክለኛ መረጃ ለእርስዎ መስጠት ነው።

ይህ የመረጃ ወረቀት ስለ አገልግሎታችን ያብራራል፣ ያሉን የተለያዩ የድህረ ሞት የምርመራ አማራጮች፤ የት እንደሚከናወኑ እና ልጅዎ በደህና እንዲወለድ ማድረግ የምንችለው እንዴት እንደሆነ ዝርዝር መረጃን ያቀርባል።

እርስዎ እርግጠኛ ያልሆኑበት ነገር ካለ፣ ወይም በበለጠ ዝርዝር ማብራሪያ እንዲሰጥበት ከፈለጉ፤ እባክዎ ይህ መረጃ ወረቀት ላቀረበልዎ ሰው ከመጠየቅ ወደኋላ አይበሉ።

ስለ ድህረ ሞት የሚከናወነው ነገር ከመወሰንዎ በፊት የሚያስፈልግዎን መረጃዎች በሙሉ ማግኘቱ አስፈላጊ ነው። ስለዚህ ጉዳይ ከቤተሰብዎ ጋር መወያየት ያስፈልግዎት ይሆናል ።

በተጨማሪም መንፈሳዊ ወይም ባህላዊ መመሪያ እና ድጋፍ ለመፈለግ ወይም ተሞክሮ ካለው ወላጅ ጋር ለመነጋገር ይፈልጉ ይሆናል (bereavement resources (የሐዘኑ መገልገያ) QR ኮድ በገጽ 4 ላይ ይመልከቱ)።

## Victorian Perinatal Autopsy Service (የቪክቶሪያ የወሊድ ግዜ/ፔሪናታል የአስከሬን ምርመራ አገልግሎት) ማን ነው?

Victorian Perinatal Autopsy Service (የቪክቶሪያ የወሊድ ግዜ/ፔሪናታል የአስከሬን ምርመራ አገልግሎት) (VPAS) በቪክቶሪያ ማህበረሰብ ውስጥ ለየወሊድ ግዜ ሞት የአስከሬን ምርመራ አገልግሎት ይሰጣል። የወሊድ ግዜ ሞት (Perinatal deaths) ሞተው የሚወለዱት ህጻናትንና ከተወለዱ በኋላ የሚሞቱትን ያካትታል። ሞቶ የሚወለድ ህጻን (stillbirth) የሚባለው አንድ ህጻን ከ20 ሳምንታት እርግዝና በኋላ ያለ ምንም የህይወት ምልክት ሲወለድ ወይም የእርግዝናው ርዝመት ካልታወቀ ከ400 ግራም በላይ ሲመዝን ነው። ከወሊድ በኋላ ሞት (Neonatal death) አንድ ህጻን በመጀመሪያ 28 ቀናት የህይወት ዘመኑ ውስጥ ሲሞት ነው።

VPAS የተቋቋመው በቪክቶሪያ መንግሥት ሲሆን በሮያል ሴቶች ሆስፒታል፣ በሞናሽ ጤና፣ በሴቶች መርስይ ሆስፒታል እና በየደም ምርመራ (ፓቶሎጂ) አቅራቢዎቻቸው መካከል ትብብር ነው።

ህጻንን በሞት ልጆቻቸውን ያጡ ቤተሰቦች ለመርዳት ከየቪክቶርያ ሆስፒታሎች ጋር ተቀራርበን እንሰራለን።

ለሆስፒታሉ ሰራተኞች መረጃ እና መመሪያ እንሰጣለን፣ እንዲሁም የአንድን ህጻን ሞት ተከትለው የሚጠየቁ የድህረ ሞት ምርመራዎች እናስተባብራለን።

# የድህረ ሞት ምንድን ነው?

የድህረ ሞት ማለት አንድ የህክምና ባለሙያ ለሞተ ሰውነት የህክምና ምርመራ ሲያደርግ ነው። ሁሉም የወሊድ ግዜ የድህረ ሞት ምርመራዎች በአንድ የወሊድ ግዜ ምርመራ ባለሙያ (perinatal pathologist) ይካሄዳሉ።

እነዚህ በየድህረ ሞት ምርመራ ለህጻናት በልዩ የሰለጠኑ፣ ከፍተኛ ችሎታና ልምድ ያላቸው ዶክተሮች ናቸው፤ ።

ማንኛውንም ዓይነት የድህረ ሞት ምርመራ ያለ እርስዎ ፈቃድ አይደረግም። የእርስዎ ውሳኔ ከሞት በኋላ የወሊድ ምርመራ ቅጽ ለVPAS ስምምነት መስጫ (VPAS consent for perinatal post-mortem examination form) ላይ መመዝገብ አለበት።

ምርመራው ከልጅዎ ሞት በኋላ በተቻለ ፍጥነት ይከናወናል። አብዛኛውን ጊዜ ይህ የሚሆነው በጥቂት የሥራ ቀናት ውስጥ ነው።

ልጅዎ ወደ ልዩ ባለሙያ/ስፔሻሊስት ቦታ ከተወሰደበት ጊዜ አንስቶ፣ በምርመራ ወቅት እና ወደ የመረጡት የቀብር ሥነ ሥርዓት ዳይሬክተር በሚመለስበት ጊዜ ምንጊዜም በጥንቃቄና በአክብሮት ይስተናገዳል።

የድህረ ሞት ምርመራና ማንኛውም ተጨማሪ ምርመራ በአውስትራሊያና በኒው ዚላንድ የወሊድ ግዜ/ፔሪናታል ማሕበር (Perinatal Society of Australia and New Zealand) (PSANZ) መመሪያዎችን ይከተላል።

በአንዳንድ ሁኔታዎች ፣ የአንድ ህጻን ሞት ወደ ሬሳ መርማሪ አካል (ኮሮኔር) መወሰድ ወይ መተላለፍ አለበት። በዚህ ሁኔታ የድህረ ሞት ምርመራውን የማዘጋጀት ሃላፊነት የኮሮነሩ ነው። ይህ የተለመደ አይደለም፣ እርስዎንና ልጅዎን በሚንከባከቡት ሰራተኞች በኩል ከእርስዎ ጋር ይነጋገሩበታል።

# የድህረ ሞት ምርመራ ለምን እናቀርባለን?

አንድ ህጻን ሲሞት ምክንያቱን ለማወቅ የድህረ ሞት ምርመራ እናቀርባለን

እንደ እርግዝናዎ ሁኔታ፣ የድህረ-ሞት ምርመራ ህጻኑ ከመወለዱ በፊት ተመርምረው የተገኙ ማናቸውም ሁኔታዎችና የሞት መንስኤ ተጨማሪ ጠቃሚ መረጃ ለማግኘት ሊረዳ ይችላል።

በተጨማሪም ለወደፊት እርግዝናዎች ጠቃሚ መረጃ የሚሰጥ ከመሆኑም በላይ ከመወለድ በፊትና በኋላ የሚከሰቱ ሞቶችን ለመከላከል የሚደረገውን ምርምር ይደግፋል።

# የተለያዩ ዓይነቶች የድህረ ሞት ምርመራዎች ምንድን ናቸው?

የተለያዩ ዓይነቶች የድህረ ሞት ምርመራዎች አሉ፣ እያንዳንዳቸው የተለያዩ የዝርዝር መጠኖች ይሰጣሉ። የበለጠ ጥልቀት ያለው ምርመራ ባካሄድን መጠን መረጃው ይበልጥ ትክክለኛ ይሆናል።

ሁሉም የድህረ ሞት ምርመራዎች በክሊኒካዊ ፎቶግራፍ ማንሳትና እንግዴ ልጁን መመርመር ያካትታል። በተጨማሪም እንደ ራጂ/ኤክስሬይ፣ ኤምአርአይ ስካን (ውስጣዊ ምስሎችን በዝርዝር የሚያሳዩ) እንዲሁም ለኢንፌክሽንና ለጄኔቲክ (ዘር ነክ) ሁኔታዎች ምርመራ ማድረግ ይችላሉ።

## ሙሉ የድህረ ሞት ምርመራ

ሙሉ የድህረ ሞት ምርመራ የልጅዎን ሰውነት ውጫዊም ሆነ ውስጣዊ ምርመራ ማድረግን ያካትታል። የፓቶሎጂስት ባለሙያ ውስጣዊ ምርመራ በሚያደርግበት ጊዜ አብዛኛውን ጊዜ ሁለት መክፈቻዎችን በማድረግ የሰውነት ክፍሎችንና አንጎልን በጥንቃቄ ያስወግዳሉ እንዲሁም ይመረመራሉ። ጥቃቅን የህዋሳት ናሙናዎች (እንደ የህዋስ መቁረጥ/ባዮፕሲ) ለምርመራ እና ለማስቀመጥ ይወሰዳሉ። አንጎልን ጨምሮ ለምርመራ የማያስፈልግ ማንኛውም ህብረህዋስ/ቲሹ ወይም የሰውነት ክፍል፣ እርስዎ ሌላ ነገር ካልጠየቁ በስተቀር፣ ወደ ልጅዎ አካል ይመለሳል።

ምርመራ ከተደረገ በኋላ የተቆራረጡት/የተከፈቱት በጥንቃቄ ይዘጋሉ፤ ልጅዎ ደግሞ ልብስ መልበስ ይችላል። አንዴ ልብስና ቆብ ከለበሱ በኋላ የተሰፉት ቁስሎች አይታዩም።

## የተወሰነ የድህረ ሞት ምርመራ

በተወሰነ የሚከናወነው የድህረ ሞት ምርመራ፤ ከሙሉ የድህረ ሞት ምርመራ አንዳንድ ክፍሎች ብቻ ይካሄዳሉ።

ፓቶሎጂስቱ የልጅዎን ሰውነት ውጨኛ ክፍል በጥልቀት ይመረምራል። ከዚያም በእርስዎና ሀኪምዎ ውሳኔ መሰረት የተወሰኑት የሰውነት ክፍሎች ወይም አካባቢዎች የተወሰነ ውስጣዊ ምርመራ ያደርጋሉ።

ለምሳሌ፣ የውጪውን ክፍል ብቻ እንዲመረመር ሊመርጡ ይችላሉ፣ ከውስጥ ደግሞ በሆድ እቃ ውስጥ ያለውን የሰውነት ክፍል ብቻ እንዲመረመር። ወይም ደግሞ፣ ለዘር/ጄኔቲክ ምርመራ ተብሎ የቆዳ ናሙና ብቻ ለመውሰድ እንዲወሰድ ሊስማሙይችላሉ።

ትናንሽ የህብረ ህዋስ ናሙናዎች ለምርመራና ለመቀመጥ ይወሰዳሉ።

## ከውጪ የሚደረግ የድህረ ሞት ምርመራ

ውጫዊ የድህረ ሞት ምርመራ ማድረግ የልጅዎን የውጭ የሰውነት ክፍል በጥልቀት መመርመርን ያካትታል። ውስጣዊ የአካል ምርመራ የለም፣ መቁረጥም የለም፣ የህብረ ህዋስ ናሙናዎች የሚወሰዱ የሉም።

## ከድህረ ሞት ምርመራ በኋላ ህብረ ህዋሱና የአካል ክፍሎች ምን ይሆናሉ?

የወሊድ ግዜ ፓቶሎጂስት ከድህረ ሞት ምርምራ በኋላ በአጉሊ መነጽር የተነሱትን ጥቃቅን ህብረ ህዋሳትን ይመረምራል።

እነዚህ ናሙናዎች አብዛኛውን ጊዜ በሰም የተሰሩ ሳጥኖች ውስጥ ተጠብቀው ይቆያሉ። አንዴ ከተመረመሩ በኋላ በፓቶሎጂ ክፍል ውስጥ ይቀመጣሉ።

ሆስፒታሎች በድህረ ሞት ምርመራ ግዜ የሚወሰደውን ማንኛውንም ህብረ ህዋስ (የሰም ሳጥኖች) ቢያንስ ለ25 ዓመታት እንዲይዙ በህጉ መሰረት ይጠየቃሉ።

በተጨማሪም አንድ አነስተኛ የህብረ ህዋስ ናሙና በረዶ እስከሚኖን ይቀዘቅዝና እርስዎም ሆኑ ሀኪምዎ አስፈላጊ ብላችሁ ለምትወስኑት ለመጪው ምርመራዎች ይቀመጣል።

የቀሩት ህብረ ህዋሳት ወይም የሰውነት ክፍሎች በሙሉ ወደ ልጅዎ አካል ይመለሳሉ። ይሁን እንጂ አንዳንድ ጊዜ በጣም ትንንሽ የአካል ክፍሎች ያሏቸው ትናንሽ ህጻናት ለምርመራ የሚበቃ ናሙና ለማግኘት መላው የሰውነት ክፍል ያስፈልገን ይሆናል።

ሆስፒታሉ የቀሩትን ህብረ ህዋሳት ወይም የሰውነት ክፍሎች ለምርምርና ለማስተማር እንዲጠቀምበት ፈቃድ ከሰጡ፣ በሰም ሳጥን ውስጥ የሚገኙትን ህብረ ህዋሳት፣ ኣዲስ ህብረ ህዋሳትና ክሊኒካዊ ፎቶግራፎችን ሊያካትት እንደሚችል አባክዎ ይወቁ። ልጅዎ በእነዚህ ነገሮች ማንነቱ ተለይቶ አይታወቅም።

የሚፈልጉ ከሆነ ከምርመራ በኋላ ህልውናዎ ሊመለስልዎት ይችላል። የማህጸን ውስጥ ምርመራ ለማድረግ ትንሽ ናሙና መውሰድንና የሬሳ ማድረቂያ ኬሚካል (የማህጸ እምብርትን ክፍል ጠብቆ ለማቆየት የሚረዳ ኬሚካል) መጠቀምን ያካትታል።

## የድህረ ሞት ምርመራ ያለው ጥቅምና ጉዳት ምንድን ነው?

### ጥቅሞች/ጠንካራ ጎኖች

የድህረ ሞት ምርምርራ ሊረዳ የሚችለው:

- ስለ ሞት መንስኤ ወይም ለሞት መንስኤ ያልሆነውን ለማግለል መረጃ ለማቅረብ።
- የልጅዎን የእርግዝና እድሜ ለማረጋገጥ።
- የልጅዎን ጾታ ለማረጋገጥ።
- የሞቱበትን ጊዜ በግምት ለማስቀመጥ።
- የጄኔቲካዊ ወይም የአካላዊ ችግሮች ኣስፈላጊነት/ድርሻ ለማስረዳት።
- ለወደፊት እርግዝናዎች ግምት ውስጥ መግባት ያለባቸው መረጃዎች ለማቅረብ።
- በወሊድ ግዜ የሚከሰት በሞት ማጣት ዙሪያ የሚደረግ ምርምር ኣሃዛትና መረጃዎች ያቀርባል፣ ሌሎች ቤተሰቦችን እና ህጻናትን ለወደፊት ለማገዝ።

### ደካማ ጎኖች

- የድህረ ሞት ምርመራ ሁልጊዜ አንድ ለየት ያለ የሞት መንስኤ ላያቀርብ/ላይነገር/ላያስታውቅ ይችላል።
- አልፎ አልፎ የድህረ ሞት ምርመራው በሚደረግበት ጊዜ ውስብስብ የሆኑ ምርመራዎች ማድረግ ማለት፣ ልጅዎ ረዘም ላለ ጊዜ መቆየት ኣለበት ማለት ነውና የቀብር ሥነ ሥርዓቱ እንዲዘገይ ሊያደርግ ይችላል። እነዚህን ምርመራዎች መቀጠል ኣለመቀጠል መወሰን ይችላሉ፤ የእርስዎ የጤና ጥበቃ ቡድን ደግሞ ምን ያህል ጊዜ ሊወስድ እንደሚችል ሊያብራሩልዎት ይችላሉ።
- ውስጣዊ የአካል ምርመራ ከተካሄደ በኋላ፣ ልጅዎ የተሰፋ ቆዳ ይኖረዋል፤ ይሄ ግን ልጅዎ ልብስ ሲለብስ አይታዩም።
- አንዳንድ ቤተሰቦች ሙሉ የድህረ ሞት ምርመራ ከተደረገለት በኋላ ልጃቸው የሚሰማው ስሜት ልዩነት እንዳለ ያስተውላሉ።

## የድህረ ሞት ምርመራው የሚከናወነው የት ነው?

በቪክቶሪያ የድህረ ሞት ምርመራ ከሶስት ልዩ ባለሙያ ስፔሻሊስት ቦታዎች በአንዱ ላይ ምርመራ ይካሄዳል፤ ልጅዎ የሞተበትን ቦታ መሰረት በማድረግ። እነዚህ ቦታዎች በሙሉ በሜልበርን ውስጥ ይገኛሉ። እነዚህም፡

- The Royal Women's Hospital, Parkville (Royal Children's Hospital Pathology) (ሮያል የሴቶች ሆስፒታል፤ ፓርክቪል (ሮያል የልጆች ሆስፒታል ፓቶሎጂ))
- The Mercy Hospital for Women, Heidelberg (Austin Pathology) (የሴቶች መርስይ ሆስፒታል፣ ሃይደልበርግ (ኦውስቲን ፓቶሎጂ))
- Monash Health, Clayton (Monash Pathology) (ሞናሽ ጤና ጥበቃ፤ ክላይተን (ሞናሽ ፓቶሎጂ))

የሚንከባከብዎ ሰራተኛ የትኛው ሆስፒታል ልጅዎን እንደሚመረምር ያሳውቅዎታል።

## ልጄን ለምርመራ የሚወስደው ማን ነው?

ህጻናትን በመንከባከብ ልምድ ያለው እና የሰለጠነ የትራንስፖርት ቡድን አለን።

ለልጅዎ የድህረ ሞት ምርመራ እንዲደረግለትከወሰኑ የእኛን ቡድን ልጅዎ ወዳለበት ሆስፒታል እንልካለን። ልጅዎ ለጉዞ ዝግጁ መሆኑን እና ለምርመራ በደህና መምጣቱን ያረጋግጣሉ።

የሚኖሩት በቪክቶሪያ ገጠራዊ ክልል ውስጥ ከሆነ በቀብር ሥነ ሥርዓት ላይ እንዲረዳዎ ለመረጡት የቀብር ሥነ ሥርዓት ዳይሬክተር ምርመራ ከተደረገ በኋላ ልጅዎ ወደ ዳይሬክተሩ እንዲመለስም ዝግጅት እናደርጋለን።

ይህ አገልግሎት በነጻ ነው፡

## የድህረ ሞት ምርመራው ምን ያህል ጊዜ ይፈጃል?

የድህረ ሞት ምርመራው የሚጀምረው እንደ ራጂ/ኤክስሬይ ወይም ኤምአርአይ (MRI) ባሉ የውጫዊ ምርመራዎች ነው። እነዚህ ምርመራዎች በተቻለ ፍጥነት ይደረጋሉ፣ ግን እነዚህ አገልግሎቶች በሚገኙበት ጊዜ በመመስረት ጥቂት ቀናት ሊወስድ ይችላል። እነዚህ ምርመራዎች ከተጠናቀቁ በኋላ ውስጣዊ ምርመራው (የቀዶ ጥገና ሂደት) ማድረግ ይቻላል። ውስጣዊ ምርመራ ሶስት ሰዓት ገደማ ይፈጃል።

ይህ ለልጅዎ የቀብር ሥነ ሥርዓት ባለዎት እቅድ ላይ ተጽዕኖ ሊያሳድር ስለሚችል ልጅዎ በእኛ እንክብካቤ ውስጥ ለምን ያህል ጊዜ እንደሚቆይ ማወቅ ለርስዎ አስፈላጊ እንደሆነ እናውቃለን። ሌላው ሊያስቡበት የሚገባ ነገር እርስዎም ሆኑ ልጅዎ የት እንደምትኖሩ ነው። በቪክቶሪያ የገጠር ክልል ውስጥ ከሆኑ፣ ልጅዎን በሜልበርን ውስጥ ወደ የወሊድ ጊዜ ፓቶሎጂስት ለማጓጓዝ የሚያስፈልገው ጊዜም ግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልገናል።

የእርስዎ ተንከባካቢ ሰራተኞች ልጅዎ መቼ እንደሚመለስልዎት ይበልጥ ትክክለኛ የሆነ መረጃ ለማግኘት የVPAS አስተባባሪን ማነጋገር ይችላሉ።

## ከድህረ ሞት ምርመራ በኋላ ምን ይደረጋል?

ድህረ ሞት የተደረገው ምርመራ ሲጠናቀቅ በቀብር ሥነ ሥርዓቱ ላይ እንዲረዳዎ የመረጡትን የቀብር ሥነ ሥርዓት ዳይሬክተር እናነጋግረዋለን።

ልጅዎ ከእኛ እንክብካቤ በደህናና በአክብሮት ወደ እነርሱ እንዲዛወር እናስተባብራለን።

## ከድህረ ሞት ምርመራ በኋላ ልጅዎን ማየት ይችላሉን?

አዎ፡ አንዳንድ ወላጆች ከድህረ ሞት ምርመራ በኋላ ከልጃቸው ጋር ጊዜ ለማሳለፍ ይመርጣሉ፣ ልጃቸው በቀብር ሥነ ሥርዓት ዳረክተር እንክብካቤ እያሉ አሊያም አንዳንድ ጊዜ በራሳቸው ቤት ውስጥ።

## የድህረ ሞት ምርመራ ውጤት የምታገኙት መቼ ነው?

ከሞት በኋላ የወሊድ ፓቶሎጂስት ምርመራ ከተካሄደ በኋላ ያገኙትን ነገር የሚያብራራ ዝርዝር ዘገባ ይጽፋል።

አብዛኛውን ጊዜ ሪፖርቱ ከ10 እስከ 12 ሳምንት ባለው ጊዜ ውስጥ ይጠናቀቃል፤ በሚያስፈልጉት ምርመራዎችና ውጤቱን ለማግኘት ምን ያህል ጊዜ ይፈጃል በሚለው ይወሰናል።

ሪፖርቱ ወደ ለእርስዎና ልጅዎን ለሚንከባከበው ሀኪም ይላካል። ልጅዎ ከድህረ ሞት በተደረገው ምርመራ ወቅት ምን እንደተገኘ ለመወያየት ከእርስዎ ጋር ተከታይ ቀጠሮ ያቀናጃሉ።

## ምን ያህል ወጪ ይጠይቃል?

የድህረ ሞት ምርመራ ምንም የሚከፈል የለውም። ወጪው በ VPAS የተሸፈነ ነው።

እኛ በተጨማሪ ልጅዎን ለምርመራ ወደ ልዩ ባለሙያ ስፔሻሊስት ቦታ ለማጓጓዝ እና ህጻናትን ከክልሉ ገጠር መኖሪያ ቦታዎች ለማምጣት የሚያደርጉትን ወጪ እንሸፍናለን።

## መወሰን ያለብዎት መቼ ነው?

የእርስዎ ጤና ጥበቃ ቡድን ልጅዎ ከሞተ ብዙም ሳይቆይ የድህረ ሞት ምርመራ ስለማድረግ ያነጋግርዎታል። ይህን ውሳኔ በተቻለ ፍጥነት መውሰዱ በጣም ኣስፈላጊ ነው፣ ጊዜ በመጠበቅ የምርመራውን ውጤት ትክክለኛነት ሊነካው ይችላል።

ከልጅዎና ከቤተሰብዎ ጋር ጊዜ ወስደው ለእርስዎ ትክክል የመሰለዎትን ይምረጡ።

## ተጨማሪ መረጃ

እነዚህን QR ኮዶች ስካን በማድረግ ለነዚህ መረጃ ያገኛሉ፡

**የአስከሬን ምርመራ በወሊድ ጊዜ ለሚሞቱ ልጆች።**

**በሐዘን ጊዜ የሚጠቅሙ መረጃዎች**

## ተጨማሪ ዝርዝር ማብራሪያ ካስፈለግዎት የ VPAS አስተባባሪን ያነጋግሩ

**T** 1800 841 024

**E** VPAC@thewomens.org.au

**ሰዓታት**
ከሰኞ እስከ ዓርብ
ከጥዋቱ 9:00am እስከ ከሰዓት በኋላ 5:00pm።